# ህሊናውን ያፅዳ

ተግባሩ ዲያቢሎስ ፣ ሸርዳጅ በምላሱ
ኑሮን የሚመራ ፣ ተጣልቶ ከራሱ
ቃሉና ተግባሩ ፣ እየተጣረሱ
የሚጨበጥ የለው ፣ ቀጣፊ መቀሱ
ዞር ብለው ከኦነግ ፣ እየተላላሱ
ለህዝብ መፈናቀል ፣ ሞት እየደገሱ
በየመድረኩ ላይ ፣ የሚቅለሰለሱ
ከነገደ ይሁዳ ፣ ያልሆኑት ንጉሱ
አሪቲ ሆነና ፣ እነሱ ሲፈሱ
ቤቱን ሳያፀዳ ፣ ለፅዳት ተነሱ ።

ሆዳም ሲፈተፍት ፣ የበላ ይመስለዋል
እንዲህማ አትናቀው ፣ የህዝቡን ማስተዋል
ባስተሳሰብ ካንተ ፣ እጅግ እርቀዋል
የዘውግ አሰራርክን ፣ ታዝበው ንቀዋል
ከጠረግክ ኦነግን ፣ ጥረገው ብለዋል
በሴራ አካሄድህ ፣ ባንተው ተሳልቀዋል ።

ኦነጉ መሪያችን ፣ ፅዳት ከጀመሩ
የጦር አዛዦችህ ፣ እነ ሚኒስትሩ
የመስሪያ ቤት ሹሞች ፣ ውጪ አምባሳደሩ
ዝቅ ብሎ እስከታች ፣ በየጉራንጉሩ
አንድ ዘውግ ፣ አንድ ጎጥ ፣ መርጠው እያጎሩ
ተጨንቀው ተጠበው ፣ ቃላት ቢያሳምሩ
በተራ አራዳነት ፣ ቢሉት እሹሩሩ
አለ ርህራሄ ፣ ፈንጂ እየቀበሩ
ይመኟታል እንጂ ፣ አይገኝም ፍቅሩ
ፅዳት ከተባለ ፣ ከቤት ይጀምሩ
እንዲያው በንቶ ፈንቶ ፣ ሰው እያደንቁሩ ።

አገሪ ኢትዮጵያን ፣ በላት መሰል ቡዳ
ማተብ ያለው ጠፍቶ ፣ መጣብን ቀዳዳ
መቼም አልተማረው ፣ ከጅማ አባ ገዳ
ሰባተኛው ንጉስ ፣ የኢትዮጵያ ይሁዳ
ሶስቴ ዶሮ ሳይጮህ ፣ ዜጋውን የከዳ
አራት ኪሎ ያለው ፣ የበሸቫ አራዳ
በቅደም ተከተል ፣ ነገር ከተረዳ
እስቲ መጀመሪያ ፣ ህሊናውን ያፅዳ ።

ታዛቢው

April 14, 2019